**በፖስታ የተላከ የ WIC ካርድ ደብዳቤ**

(Mailed WIC Card Letter)

ቀን፡-

ለ፡-

ውድ

በልዩ ሁኔታዎች ምክንያት፣ የ WIC ካርድዎን ለእርስዎ በፖስታ እየላክልንዎት ነው።

የ WIC ካርድዎን ለመጠቀም እባክዎን እነዚህን ደረጃዎች ያስታውሱ፡-

1. የእርስዎን ባለ 4-አሃዝ PIN ማወቅዎን እርግጠኛ ይሁኑ።
   - የይለፍ ቃልዎን ካላስታወሱ፣ በማንኛውም ጊዜ፣ በቀን ወይም በማታ ዳግም ለማስጀመር ወደ 1-844-359-3104 ይደውሉ።
   - ካርዱን የሚይዘውን ሰው የልደት ቀን እና ዚፕ ኮድ ያስገቡ።
2. ካርድዎ ላይ ምን ዓይነት የ WIC ምግቦች እንዳሉ ይመልከቱ።
   - የ WICShopper መተግበሪያን ይጠቀሙ።
   - ከካርዱ ጋር የግብይት ዝርዝር ተያይዞ ከሆነ ይመልከቱ።
   - የመጨረሻ የ WIC ሸቀጥ መደብር ደረሰኝዎን ይመልከቱ።
   - የመደብር ደንበኛ አገልግሎቶችን ይጠይቁ።
   - ወደ WIC ክሊኒክ ይደውሉ።
3. ግብይት ለመፈጸም ባሉት በመጀመሪያ እና በመጨረሻ ቀን ወይም በመካከል የ WIC ምግቦችን ይግዙ።
   - ያልገዟቸው ማንኛውም ምግቦች፣ ወደ ቀጣዩ የጥቅማ ጥቅም ወር አይተላለፉም።
4. የ WIC ፈቃድ ባላቸው መደብሮች ብቻ ይሸምቱ። የ "WIC Accepted Here (እዚህ WIC ን እንቀበላለን)" የሚሉ ምልክቶችን ይፈልጉ።
5. እርስዎ ያልዎትን የምግቦች መጠኖች እና ዓይነቶች ብቻ ይግዙ።
6. የ WIC ካርድ መጠቀምዎን ለገንዘብ ተቀባዩን አሳውቁ።
7. በሚጠየቁበት ጊዜ ካርድዎን ይጠቀሙ እንዲሁም የእርስዎን ባለ 4-አሃዝ PIN ያስገቡ።
8. ደረሰኝዎን ይያዙ።

ለሚከተሉት ለማንኛውም ምክንያቶች ከታች ባለው ቁጥር እባክዎ ለክሊኒክ ሰራተኞች ይደውሉ፡-

- ስለ WIC ካርድዎ ወይም ስለሚገኙት ምግቦች ጥያቄዎች ካልዎት።
- መደብሩ ላይ የ WIC ካርዱን ሲጠቀሙ ችግር ካጋጠምዎት።
- ቀጣይ የ WIC ቀጠሮዎን መያዝ ወይም መቀየር አለብዎት።

የእርስዎ WIC ክሊኒክ፡

## በፖስታ የተላከ የ WIC ካርድ ደብዳቤ

(Mailed WIC Card Letter)

**WIC መድልዎ አያደርግም።**

ከፌደራል የሲቪል መብቶች ሕግ እና የዩናይትድ ስቴትስ የእርሻ መምሪያ [U.S. Department of Agriculture (USDA)] የሲቪል መብቶች ደንቦች እና ፖሊሲዎች ጋር በተያያዘ፣ ይሄ ተቋም በዘር፣ በቆዳ ቀለም፣ በትውልድ አገር፣ በጾታ (በጾታ ማንነት እና በወሲብ አዝማሚያ ጨምሮ)፣ በአካለስንኩልነት፣ በዕድሜ መሰረት አድሎ እንዳያደርጉ ወይም ከዚህ ቀደም ለተሳተፉበት የሲቪል መብቶች እንቅስቃሴ የተነሳ የበቀል ወይም የአፀፋ እርምጃ እንዳያከናውኑ ይከለክላል።

የፕሮግራሙ መረጃዎች ከእንግሊዘኛ ቋንቋ በተጨማሪ በሌሎች ቋንቋዎች እንዲሰጡ ይደረጋሉ። የፕሮግራሙን መረጃ ለማግኘት የተለየ የመግባቢያ ዘዴ የሚያስፈልጋቸው አካለ ስንኩላን ሰዎች (ለምሳሌ እንደ ብሬል፣ በትልቅ ፊደል ሕትመት፣ የድምጽ ቅጂዎች፣ የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ)፣ ፕሮግራሙን የሚያስተዳድሩ የግዛት ወይም የአካባቢው ኤጀንሲዎች ጋር በመሄድ ወይም ደግሞ የ USDA'ን TARGET ማዕከል በ (202) 720-2600 (በድምጽ እና TTY) ደውለው ማግኘት ወይም በፌደራል ሪሌ ሰርቪስ (Federal Relay Service) (800) 877-8339 በኩል USDA ን ደውለው ማግኘት አለባቸው።

በፕሮግራሙ ላይ የተፈጠረ የአድሎ ሁኔታን አቤቱታ ለማቅረብ፣ ቅሬታ አቅራቢዎቹ የ USDA መርሀግብር የአድሎ አቤቱታ ማቅረቢያ ቅጽ የሆነው ቅጽ AD-3027 መሙላት አለባቸው፣ ቅጹ ኦንላይን በዚህ አገናኝ፡- https://www.fns.usda.gov/sites/default/files/resource-files/ad3027-amharic.pdf ፣ ወይም ከማንኛውም የ USDA ቢሮ፣ በ (866) 632-9992 ላይ በመደወል፣ ለ USDA የሚላክምደብዳቤ በመፃፍ ማግኘት ይችላል። ደብዳቤው የአቤቱታ አቅራቢውን ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥር፣ እና ተፈጽሟልምየተባለውን የሲቪል መብቶች ጥሰት ሁኔታ እና ቀን፣ ጉዳዩን የሚመለከተውን የሲቪል መብቶች ምክትል ሴክረታሪ[Assistant Secretary for Civil Rights (ASCR)] መጥቀስ፣ ተፈጽሟል የተባለውን የአድሎ አሰራር በቂ በሆነም ሁኔታ በዝርዝር ማስፈር አለበት። የተሞላው የ AD-3027 ቅጽ ወይም ደብዳቤ ለ USDA በሚከተለው አድራሻ መቅረብም አለበት፡-

1. **በደብዳቤ፡-**
   U.S. Department of Agriculture
   Office of the Assistant Secretary for Civil Rights
   1400 Independence Avenue, SW
   Washington, D.C. 20250-9410; ወይም
2. **ፋክስ፡-**
   (833) 256-1665 ወይም (202) 690-7442፤ ወይም
3. **ኢሜይል፡-**
   program.intake@usda.gov

ይሄ ተቋም ሁሉንም ደንበኛ በእኩሌታ የሚመለከት ነው።
WIC መድልዎ አያደርግም።

ይህንን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለመጠየቅ፣ 1-800-841-1410 ላይ ይደውሉ።
መስማት የተሳነዎት ወይም የሚያስቸግርዎት ደንበኞች ከሆኑ፣ እባክዎ ወደ 711 (Washington Relay) ይደውሉ ወይም ወደ wic@doh.wa.gov ኢሜይል ይላኩ።

DOH 960-367 October 2023 Amharic